# ዘረኝነትና እንድምታው

ሓጎስ ኣረጋይ (PhD) ነሃሴ. 30፣ 2009

በእርግጥ ሰዎች ነገሮችን የሚረዱበት ኣገባብ የተለያዩ ሊሆን ይችላል። የሰዎች ኣመለካከትም እንዲሁ ። ሆኖም ግን የተለያየ ኣመለካከት የመኖሩን ያህል በጋራ መራመድ የሚያስችሉን የጋራ ኣስተሳሰቦችና እሴቶች እንዳሉንም ከኣለማችን የምንረዳው ሃቅ ነው። ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ከ 100,000000 (ከንድ መቶ ሚልዮን) በላይ የሚገመት ህዝብ እና ወደ ሰማንያ ቋንቋ ኣካባቢ የሚናገሩ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እንደ ኣገር በጋራ ኣብረን እየኖርን ያለነው። እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝቦች የተለያዩ ባህል፣ ወግ እንዳላቸውም ይታወቃል። ወደ ገጠር ኣካባቢ ከዘለቅን ደግሞ ከራሳቸው ቋንቋ ውጭ በሌላ መግባባት የማይችሉ የህዝቦች ብዛት በቀላሉ የምንገምተው ኣይደለም። በኣንድ ወይም በሌላ መልኩ ኣንዳንድ ወገኖች የማህበረሰባቸው ችግር በመረዳት ስለ ማንነታቸው ፣ ባህላቸው ፣ቋንቋቸው በመሳሰሉ ጉዳዮችን መሰረት ኣድርገው ጥያቄዎችን ሲያነሱ ይስተዋላሉ።

ነገር ግን የብሄር ወይም የብሄረሰብ ጉዳይ መሰረት ኣድርገው ለሚነሱ የመብትና የተጠቃሚነት ጥያቄዎች ፣ በኣንዳንድ ወገኖች በዘረኝነት ሲፈርጁዋቸው ይስተዋላል፣ ለምን ይሆን? ከዚህ ኣንፃር ሲታይ ለዘረኝነት እየተሰጠው ያለው ትርጉም በመሰለኝ እየተገለፀ መሆኑን እንረዳለን። በእርግጥ ዘረኝነት የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በመሰለኝ የሚታለፍ ኣይደለም። ምክንያቱም ከጀርመን ናዚ ተያይዞ ኣለም ኣቀፋዊ ትርጉም ኣለው ብዬ ኣስባሎህ። በመሆኑም ዘረኝነት ምን ማለት እንደሆነ በሚከተለው መንገድ ሊገለፅ ይችላል

- Racism is a prejudice, discrimination, or antagonism directed against someone of a different race based on the belief that one's own race is superior (https://www.google.com/#q=definition+of+racism)
- የኣማርኛ ትርጉሙ በሚከተለው መንገድ ለማቅረብ ሞክሪኣሎህ፥

- ዘረኝነት (racism) በኣንድ ወይም በሌላ መልኩ ከራስህ ውጭ የሆነውን ብሄር/ዘር ማግለል፣ ኣንኳስሶ መመልከት፣ ጉዳት ማድረስ ፣ በዘር ነክና ከዘር ተያያዥነት ያላቸው ስድቦችና ዛቻዎችን ማድረስን ያጠቃልላል።

ስለዚህ ከላይ የተቀመጠውን ትርጓሜ መነሻ በማድረግ በመሪዎች ደረጃ ምን እንደተነገሩና ምን እንደተሰሩ ለማሳያነት ያክል ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ለማስቀመጥ ተሞክረዋል።

ሰንተረዥ 1: የዘረኝነት ልክፍት በቀደሞ ባለስልጣናት ሰታወስ

| **ወቅት** | **የተነገሩትና የተፈፀሙት ግፍፎችና ጭካኔዎች** | ዋቢ |
|---|---|---|
| **በዳግማዊ ሚኒሊክ** | • የትግሬ ወታደር በዚያ ጉሮሮ በሚፍቀው ቋንቋቸው ኲሪ ኲሪ እያሉ እርጉዝ አሰወረዳት እመጫት ጡቷ ደረቀባት. . . . . "<br>• "አፄ ምንሊክ ያደሩበት አገር ለምልሞ ሲያድር ትግሬ ያደረበት እንደ አንበሳ ልሶት ያድራል "<br>• ". . . . . ይህ አንበጣ ትግሪ በጠፋልን የማይል አልነበረም "<br>• ከ 400 መቶ በላይ የሚሆኑ ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑትን ሰዎች ቀኝ እጃቸውና ግራ እግራቸው ቆረጧቸው . . . .ይላል። በተመሳሳይ ሁኔታ የነበሩ የኢጣልያ ወታደሮች ግን በነፃ እንዲሰናበቱ አድርገዋል ።<br>• በግቤ፣ አዋሽ፣ ከፋ ፣ ሃረርጌ ወዘተ ብዙ የኦሮሞ፣ ወላሞ፣ ወዘተ ህዝብ እንዳለቀ ይገልፃሉ ። የድርጊቱ አስከፊነት ለመግለጽ በወቅቱ ውሻና እርግብም እንዳልቀረ በማሳያነት ይገልፃሉ (ገፅ 677)<br>• "ምኒሊክ የሰሎሞን አንበሳ . . . . . የጋላ ድልብ. . . . . ሰለቸውና የትግሬን የአንበሳ ለምድ የለበሰ መስበር ወደደ"<br>• ልጅ ሽማግሌ ሳይሉ የትግራይ ተውላጅ የሆኑትን ወንዶች እዲገደሉ ፣ እንዲሰለቡ ካልሆነም እንዲያርዱ አዘዋል፣ አስፈፅመዋልም<br>• የትግራይ ህዝብ ንብረት እንዲዘርፉ ካልቻሉ ደግሞ እንዲያቃጥሉ አስደርገዋል | በኣይጋ ፎረም "ኢትዮጵያና የዘረኝነት ልክፍት" በሚል ርእስ |
| **በአፄ ሃ/ስላሴ** | • ከየመን በሚነሱ የእንግሊዝን ኣውፕላን በመታገዝ በመቐለ ከተማ ላይ በግብይት የነበረውን ህዝብ አስፈጁት | FM 104.4 mekelle |
| **በደርግ ግዜ** | • ኢትዮጵያችን ችጋራም ተብላ የምትታወቀው ክትግራይ አካባቢ በሚመነጭ ችግር ነው<br>• ከትግራይ የምናገኘው ገቢ ለትግራይ የሚሆን ጠመኔ እንኳን ኣይሆንም. . . .<br>• **በአካባቢ የሚታዘዘው የደርግ ሰራዊት** የገበሬዎች ንብረትና ሃብት ዘርፈዋል፣ ቤት ኣቃጥላለዋል፣ ሰዎችም ገድሏል፣ እርጉዞች በሳንጃ ወግቶ ገድሏል፣<br>• በማእከል የሚታዘዝ ደግሞ በቤኤም ፣ በኣውሮፕላን ወዘተ ለ 17 ዓመታት ያህል የትግራይን ህዝብ ኣሰቃይተዋል። ለምሳሌ ሃውዜን ከተማ ላይ በገብያተኛው ህዝብ በኣንድ ጀምበር ከ 2500 ሰዎች በላይ በኣውሮፕላን ጨፍጭፈዋል። | በኣይጋ ፎረም "ኢትዮጵያና የዘረኝነት ልክፍት" በሚል ርእስ |

የፌዴራል መንግስት ለኣገራችን ኣዲስ በመሆኑ ወይም ደግሞ ጥቅማቸው ስለተነካባቸው ነው መሰለኝ ለኣንዳንድ ወገኖች ኣይመቻቸውም። በመሆኑም በብሄር ብሄረ ሰብ መደራጀትን የጎሪጥ ያዩታል። ዘረኛ ኣደረጃጀት ይሉታል። ከዚህ የምንረዳው ምናልባት ቢበዛ በዳግማዊ ኣፄ ሚኒሊክ የተፈጠረው የኣማራ የገዢ መደብ ልእልና (hegemony) ያጠላባቸው ይመስለኛል።

እንደሚታወቅው በዳግማዊ ኣፄ ሚኒሊክ የኣመራር ግዜ ከኣማራ ተውላጆች በስተቀር ያልተጨፈጨፈ ብሄር ወይም ብሄር/ብሄረ ሰብ ነበር ለማለት ኣያስደፍርም። የንግስነታቸው ቁርሾም በሸዋ መኳንንት ይመራ እንደነበር ማስረጃዎች ያሳያሉ። ከዚህ በተጨማሪ በየኣከባቢ የነበረውን የነገስታትን (ንጉስ ጎጃም ወዘተ) ስልጣን በማንኮታኮት በማእከል የሚመራ መንግስት ኣቋቋሙ። የትግራይን ጉዳይ በምሳሌነት ብንወስድ ትግራይን በሶስት የኣስተዳደር ወሰን በመከለልና

ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለኣፄ ሚኒሊክ የሆኑ ሶስት እንደራሴ በማስቀመጥ በፈለጉት ኣቅጣጫ መምራት ቻሉ። ዘርን መሰረት ኣድርገው በፈፀሙት ግፍና ጭፍጨፋ ተመስርተው የኣማራ ገዢ መደቦችን ልእልና (hegemony) ማስፈን ቻሉ። ከኣፄ ሚኒሊክ በኋላም ቢሆን የኣማራ የገዢ መደብ የበላይነት መዘውር በመቀጠሉ በሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ላይ የአስተሳሰብ ፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ ጫናዎች እንደነበሩ የታሪካችን ክስተት ነው። እንዲሁም የኣማራ የገዢ መደቦች ልእልና (hegemony) በሃል/ በጉልበት በሌሎች ብሄር ብሄረ ሰቦች ላይ የተጫነ ሸክም እንደነበር ፀሃይ የሞቀው ሃቅ ነው ማለት ይቻላል ።

በመሰረቱ የኣማራ የገዢ መደቦች ልእልና (hegemony) ረዘም ላለ ግዜ ከመቆየቱ ኣንፃር የተነሳ፣ ሌሎች ብሄር ብሄረ ሰቦች ለመኖር ሲሉ ብቻ ሽንፈትን ተቀብሎ ከስርዓቱ መላመድ ኣማራጭ ኣልነበራቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። በጭቆና ቀንበር መኖራቸውን የሚያስረዳን፣ ስርዓቱ ከስር መሰረቱ ሲገረሰስ፣ በሃይል ተዳፍኖ የነበረውን ኣስተሳሰብ ጎልቶ መውጣት ጀመረ። እንዲያውም ኣንዳዶቹ ዳግም ወደ ነበረው የስርዓት ኣገዛዝ እንዳይመለሱ ስጋት ላይ መሆናቸው ኣንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ከኣንዳንድ የኣማራ ልሂቃን ነን ባዮች በስተቀር የኢትዮጵያ ህዝቦች ኣሁን ያለው ስርዓትና ህገ መንግስት እንደቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ። በመሆኑ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ-ሰቦች ሙብታቸው በመከበሩ ደስታቸው ገልፅዋል። ሌላው ይቅር በነበረው ጭቆና ቋንቋንቸው ለመጥፋት ተቃርቦ የነበረውን የህብረተሰብ ክፍል ሳይቀሩ ለሙብታቸው መከበር በመታገል ላይ መሆናቸውን ይታወቃል። ለምሳሌ የቅማንት ብሄረ-ሰብ ራሳቸው በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችላቸው ወሰን ለመካለል ኣማራና ቅማንት በሚኖርባቸው ቀበሌዎች ህዝበ ውሳኔ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ ናቸው።

ከላይ የተገለፀው እውነታ የሚያሳየን የኢትዮጵያ በሄር ብሄረ ሰቦች ተመችቶዋቸው ሳይሆን እየኖሩ የነበረው፣ ኣማራጭ በሌለው ማእቀፍ ውስጥ ሁነው የስቃይ ህይወት እየመሩ እንደነበር መገመት ይቻላል። ወይም ደግሞ ኣንድ ወቅት ሊፈነዳ በሚችል የፈንጅ ወረዳ ላይ እየተራመድን እንደነበርን በግልፅ ያሳያል።

ስለዚህ ኣንዳንድ የኣማራ ሊሂቃን እንደሚሉት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦች በኢህኣዴግ የተፈጠሩ ኣይደሉም ። ጥንትም የነበሩ፣ ኣሁንም ያሉ፣ ለውደፊትም የሚኖሩ ናቸው። በመሆኑም ብሄር ብሄረ ሰቦች በኢህኣዴግ/ወያኔ የተፈጠሩ ከማለት ይልቅ በኣማራ የገዢ መደብ ተድፍቆ የነበረውን ኣስተሳሰብ በወያኔ/ኢህኣዴግ ለምን ተጋለጠ ከሆነ ጥያቄው ያስማማናል። በእርግጥ በኣፄዎቹ ወቅት ኢትዮጵያ የምትባል ኣገር የጥቂት ገዢ መደቦች እንጂ የኢትዮጵያ ህዝቦች እንዳልነበረች በብዙ መልኩ ተገልፅዋል ( የዋለልኝ መኮነን ኣጭር ፅሁፍ በወቅቱ የነበረውን ምስል በግልፅ ያሳያል )።

> **ከነበረው ግፍና ጭቆና ያተረፍነው ነገር ቢኖር ጦርነት ( የባሌ የገበሪዎች ኣመፅ፣ የቀዳማይ ወያኔ የገበሬዎች ኣመፅ፣ ካላኣይ ወያነ ወዘተ) ነው። እንዲሁም ኣሁን ያለው ኣስተዳደር መዋቅር የነበረውን ብሄራዊና የመደብ ጭቆና መልስ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። በኣሁኑ ሰዓት ደግሞ ጥርጣሬና ስጋት ማእከል ያደረገ የጠባብነት ኣስተሳሰብ ጉልበት ማደግ ወዘተ ናቸው።**

የነበረው የኣማራ የገዢ መደብ ልእልና (hegemony) ኣሁንም ቢሆን በማወቅም ባለማወቅም ሲንፀባረቅ ይታያል። ለምሳሌ ፣

- የብሄር ብሄረ ሰቦች ጎልቶ መውጣት ለምን አስፈለገ? የሚሉ ጥያቄዎች ያነሳሉ።
- ስለ የማንነት መብት መጠየቅ፣ ማንነትን ማጉላት ወዘተ በዘረኝነት ይፈርጁታል።

በነሱ አባባል መጉላት ያለበት ኢትዮጵያዊነት ነው ይላሉ። ኢትዮጵያዊነት ከዜግነት መገለጫ ኣልፎ በባህል፣ በወግ ፣ በታሪክ እንዴት ይገለፅ ለሚለው ጥያቄ የሚሰጡት መልስ በሁለት ነገሮች ይንጠለጠላል

- የኣንደኛው ኣስተሳሰብ የሚለው፣ በነበረው የኣማራ የገዢ መደብ ልእልና የማስቀጠል ዝንባሌ ያሳያል። ለምሳሌ ኣማርኛ የስራ ቋንቋ መሆን ቀርቶ ብሄራዊ ቋንቋ እንዲሆን የመፈለግ ሁኔታ ያሳያሉ ወዘተ ። በምን ሂሳብ ነው ኣማርኛ ብሄራዊ ቋንቋ የሚሆነው? ይህ ከሆነ ደግሞ ኣጠቃላይ ባህላችን ወጋችን ሁሉ በኣማራ ህዝብ ባህል፣ ወግ ወዘተ ይተካል ማለት ነው።
- በሁለተኛው ረድፍ ኣስተሳሰብ ያለው ኣስተሳሰብ ደግሞ ፣ ሁሉም ሰው የየራሱ ባህል ያንፀባርቅ ይላሉ ፣ ነገር ግን መጉላት የለበትም ይላሉ። ኢትዮጵያን ወክሎ የሚጎላው ባህል ምን ይሁን ብትላቸው መልስ ኣይኖራቸውም።

በኣጠቃላይ የሁለቱም ኣስተሳሰብ ስንመለከት የሚያሳዩን፣

- ሆን ተብሎ በሌላው ብሄር ብሄረ ሰቦች ጫና ለመፍጠርና የማታለል ስራ ነው የሚሆነው

  ወይም ደግሞ

- ቀደም ብሎ በነበረው የኣማራ ገዢ መደብ ልእልና (hegemony) ስር የወደቁ /የተማረኩ/ በመሆናቸው በዚያው ልክ ይባንናሉ ማለት ነው።

ስለዚህ በኣንድ ወይም በሌላ መልኩ የሁለቱም ኣስተሳሰቦች የሚያመለከተው በሌሎች ብሄር ብሄረ ሰቦች ላይ ጫና እየፈጠሩ መሆኑን ያሳያል። ብንወድም ባንወድም መቀበል ያለብን ጉዳይ ግን ኣለ እላለሁ ። ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረ ሰቦች ኣገር ናት። ኢትዮጵያ በባህል፣ በውግ ወዘተ ልትወከልም፣ ልትገለፅም የሚትችለው በሁሉም ብሄር ብሄረ ሰቦች እና ህዝቦች ማንነት በሚገልፅ ስእል/መልክ መሆን ይገበዋል። ስለዚህ የብዙሁነታችንን መጉላት ለድርድር የሚቀርብ ኣለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል እላለሁ። በኔ ኣመለካከት የኢትዮጵያ ባህል ማለት የሁሉም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦችና ህዝቦች ባህልና ቁንቋ ማለት ነው እንጂ የኣማርኛና የኣማራ ባህል ብቻ ኣይደለም።

> **ስለዚህ ሌላውን ብሄር ብሄረ ሰብና ህዝቦች እስካከበረ ድረስ ኣንድ ሰው (ቡድን) ስለ ብሄሩ መናገር፣ ብሄሩ ያከበረ ፣ ብሄሩ ያሞካሸ ፣ ስለብሄሩ የመብትና የማንነት ጥያቄ ያነሳ ፣ያቀረበ ወዘተ በፍፁም ! በፍፁም ! በፍፁም ዘረኛ ሊባል ኣይገባም ፣ ኣይደለምም። ስለዚህ ወያኔ፣ ኦህዴድ ፣ ወዘተ ዘረኛ ፖለቲካ ድርጅቶች ኣይደሉም፣ ሊባሉም ኣይገባም። ይህንን የማንቀበል ከሆነ የኢትዮጵያን ብዙህነት ኣንቀበልም ማለት ነው፣ ወይም ደግሞ *ኣንድ ኣገር፣ ኣንድ ህዝብ፣ ኣንድ ሃይማኖት* የሚል ፍልስፍና እስከኣሁን በልባችን እየነገደ መሆኑን ያሳያል።**

በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ ወያኔ እንደ ዘር ኣማራን ለማጥፋት እየሰራ ነው የሚል ዲስኩር በዘሃበሻ ድህረ ገፅና መሰሎች ፖስት እየተደረጉ ናቸው። ኣንዳንዶችን ሳነብ ኣንድ ነገር ትዝ ኣለኝ ። ኣንድ ወቅት ኣቶ መለስ ዜናዊ ከፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ጋር ያደረጉት ወይይት ኣስታወሰኩኝ ። እንደሚታወቀው ኣቶ መለስ

የህወሓት/የኢህኣዴግ መሪ ሁነው ለብሄር ብሄረ ሰቦች ሙብት መከበር ብዙ የሰሩና የታገሉ ሰው ናቸው። በመሆኑም በሰማንያቹ ዓ/ም ኣካባቢ ኣቶ መለስ የኣማራ ህዝብ እንደ ህዝብ ኣለ ብለው ሲሞግቱ/ሲከራከሩ በተቃራኒው የቆሙት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ደግሞ ኣማራ የሚባል ህዝብ/ብሄር የለም ብለው ነበር የተከራከሩት ። ከዚህ በተጨማሪ የደርግ መሪ የነበሩ መንግስቱ ሃ/ማርያም 'ኣማ' ማለት በተራራ የሚኖር ህዝብ እንጂ ኣማራ የሚባል ብሄር የለም ብለው እንደነበር ይታወቃል።

ስለዚህ እንዴት ነው የኣማራ ህዝብ እንደ ህዝብ ኣለ ብለው የሚከራከሩ የህወሓት ታጋዮች የኣማራን ህዝብ ለማጥፋት ይሰራሉ ብለው ኣንዳንድ ወገኖች የሚያወሩት? " ካብ በሃሊ ይምሓርካ" የሚባል የትግርኛ ምሳሌ ኣለ። ወይም ደግሞ ሰሚ ይፍረደው ከማለት ውጭ ምን ይባላል ።

በኔ ኣመለካከት የኣብዬን. . . ለእምዬ. . . እንደሚባለው ነው የሆነው ። ምክንያቱም ከኣሁን በፊት በመንግስት ደረጃ ዘርን ማእከል ኣድርጎ ህዝብን ለማጥፋት እየሰራ የነበረው ማነው? ለሚለው መልስ ሰንጠረዥ 1 ይመልከቱ።

ኣሁንም ቢሆን በኣንዳንድ ወገኖች እየተወራ ያለው ምን ልንለው እንችላለን? ብለን ብንጠይቅ እውነታውን ለማግኘት የሚቀጥለውን ያንብቡ። ኣሁን ካለው መንግስት በተፃራሬ በሚገኙ ሃይሎች ከሚሰነዘሩት ኣስተሳሰቦች መካከል

- ✓ ኣማራን ለማጥፋት ወያኔ ከኣንድ ትውልድ በላይ እየሰራ ነው፣ በኣሁኑ ሰኣት ምርጫ የለንም መዳን ወይም ሞሞት ( በዘሃበሻ ድህረ ገፅ ኣንዱ ኣለም ተፈራ)
- ✓ የኣማራ ተኘተሃል (ሳተናው ደህረ ገጽ፥ ኣድማሱ ብጋሻው )
- ✓ በ ትእምት ያነጣጠረ ዘመቻ (ሳተናው ድህረ ገፅ ፣ ከመስከረም )። ነገር ግን እውነታው ከ 99% በላይ የኢትዮጵያ ሃብትና ኢንቨስትመንት በኣዲስ ኣበባና ኣከባቢው ነው ያለው። ትንሽዬ ፋብሪካ ትግራይ ላይ ቢቋቋም ከፋቸውና በህዝብ ያነጣጠረ ዘመቻ ያካሂዳሉ። የፋብሪካ ፀዳል የሚባል ትግራይ ላይ መታዬት የለበትም እያሉን ነው።
- ✓ ሰሜን ጎንደር ለሶስት ከፍሎ እስከ ቬንሻንጉል በመጠቅለል ታላቁዋን ትግራይ ሊመሰረት ነው (በዘሃበሻ በኣያለው )
- ✓ ሙስና የሚሰራ/ሃብት የሚያግበሰብስ ከትግራይ የመጡና በኣመራር ያሉ ግለ ሰቦች ብቻ ናቸው
- ✓ ከትግራይ ተወላጅ የሆነ ባለሃብት ብቻ በስርቅት/ሙስና የደረጀ / የፈረጠመ እንድሆነ
- ✓ በጣና ያለው እቧጭ ሆን ተብሎ በወያኔ የተሰራ ነው ( ሳተናው ድህረ ገፅ በሰኣሊ ኣምሳሉ ገ/ኪዳን ኣርጋው)
- ✓ በኢትዮጵያውያን ደም የተጨማለቀ የኣሸንዳ በኣል በመቐለ ከፋሽሽት ብሄራዊ መዝሙር እኩል ነው ( ዘሃበሻ ጌታቸው በቀለ ከኖርወይ)
- ✓ ከኣማራ ወደ ትግራይ የተወሰዱ ጀነሪተሮች (ሳተናው ኣያለው መንበር )
- ✓ የኣማራ ህልውና የሚከበረው በራሱ ትግል እንጂ በህገ መንግስቱ ኣይደለም (ዘሃበሻ ከይገርማል)
- ✓ በቀን ገኸርነት ላይ ንቀተን የደረበው ህወሓት (ዘሃበሻ ድህረ ገፅ በያሬድ ኣውግቸው)
- ✓ ትግራይ ከሌላው ማህበረ-ሰብ ተጠቃሚ እንደሆነ ያስቀምጣሉ
- ✓ በህወሓት የሚዘወር መንግስት ነው ያለው ብለው ያትታሉ

✓ ሰሙኑን ደግሞ የቅማንት የማንነት ጥያቄ በወያኔ የተሰራ ነው ይልሉ። ሌላው ይቅርና ከዚህ ኣባባል የምንረዳው የቅማንት ህዝብ ኣያስብም እያሉን ነው። ስለዚህ ከኣንዳንድ የኣማራ ሊሂቃን ነን ባዮች የምንረዳው በህዝብ ያላቸው ንቀትን ነው። ማለትም የቅማንት ህዝብ ድሮ በኣዜዎቹ እንደተሰራ ነው መቀጠል ያለበት እያሉን ነው። መጠየቅ የነበረበት ግን የቅማንት ህዝብ ለምን ይህን ጥያቄ ኣቀረበ? ለቀረበው ጥያቄ በቂ መልስ መስጠት ነው የሚያዋጣው እንጂ የሌለ ኣመክንዮ መስጠት ማንነታችንን ያጋልጣል።

ከላይ እንደተገለፀው በስነ ልቦና ላይ ጫና ለማሳዳርና ህዝቦችን ለማጋጨት እየተደረገ ያለው ትርክት ስንመለከተው ማህበራዊ ድህረ ገፆችን በእጅግ እያጨናነቀ ያለ ጉዳይ ነው። በኣንባቢውም ላይ የተለያዩ ስሜት በመፍጠር ላይ ይገኛል ብዬ ኣስባሎህ። ኣንዳንዶቹ ከእውነት የራቀ ነው ብለው ኣስተያዬት ሲሰጡ ይስተዋላሉ። ኣንዳንዶቹ ደግሞ በሚሰጠው ኣስተያዬትም ጨለምተኛ ሁነው የሚዘሙ እንዳሉ መረዳት ይቻላል።

**የሁሉም ድምር ሃሳብ ስንመለከተው ግን ትግራይና የትግራይ ተወላጅጅ/ህዝብ ከየተኛውም ብሄር ብሄረ ሰብ ለየት ባለመልኩ ተጠቃሚዎች ናቸው ፣ በስርዓቱ ልዩ ተጠቃሚ ናቸው ይላሉ ። ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ በሌላ የኢትዮጵያ ሃብት ያለ ኣግባብና በኣቋራጭ እየከበሩ ያሉ ናቸው ይላሉ ። ልክ እንደ ቀኝ ገዢ ኣድርገው ለመሳልም የሚሞክሩ ኣሉ።**

ይህ ዝንባሌ በኣንድ ወይም በሌላ መልኩ ስንመለከተው ጎጂ ነው። ምክንያቱም ከመንግስት በተቃራኒ እየተባለ ያለው፣

- **እውነት ከሆነ ለትግራይና ለትግራይ ተወላጆች/ህዝብ ይጎዳል እንጂ ኣይጠቅምም። በግዜው መፈተሽ ያለበት ጉዳይ ነው**
- **ከእውነት የራቀና የጥላቻ ትርክት ከሆነ ደግሞ በትግራይና በትግራይ ተውላጆች /ህዝብ እንዲሁም በኣማራ ህዝቦች ላይ እየታወጀ ያለ ጦርነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል**

ስለዚህ ምንም ቢሆን ምንም እየነነደ ያለው ትርክት መመርመር ያስፈልጋል ። እንግዲህ ሃሳቡን የሚያቀርቡ ሰዎች ያላቸውን ኣስተያዬት እስከኣሁን በግልፅ ማስቀመጥ ባይችሉም ኣንድ እርምጃ ተጉዘን መመርመር ያስፈልጋል እላሎህ። እንደማሳመኛ ሃሳብ ብለው የሚያቀርቡት የኣገሪቱን መንግስታዊ ስልጣን በትግራይ ተውላጆች መዘውር ውስጥ እንደሆነ ነው የሚናገሩት ።ስለዚህ በፌደራልና በክልል የመንግስት መዋቅሮችን መፈተሽ ኣንድ ነገር ሊያሳየን ይችላል ብዬ ኣስባሎህ።

እንድሚታወቀው በኣገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ያለው ኣካል “ የኢትዮጵያ የህዝብ ተውካዮች ም/ቤት” መሆኑን የኣገሪቱ ህገ መንግስት በግልፅና በማያሻማ መልኩ ያስቀምጣል።እንዲሁም የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚቋቋመው በቀጥታ በህዝብ ከየክልሉ በሚመረጡ ኣባላት መሆኑን ነው የሚያሳየው። ከየክልሉ የሚወከሉት የኣባላት ባዛትም እንደ የክልሉ የህዝብ ብዛት ይለያያል። በዚህም መሰረት ከየክልሉ የሚወከሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብዛት በሚቀጥለው ሰንጠዥ ይመልከቱ።

ሰንጠረዥ 2. ከየክልሉ የሚውከሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአባላት ብዛት የሚያሳይ

| | ትግራይ | አፋር | አማራ | ኦሮምያ | ቤንሻንጉል | ጋምቤላ | ሶማሊያ | ሃረሪ | ደቡብ ህዝቦች | አዲስ አበባ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 38 | 8 | 138 | 178 | 9 | 3 | 23 | 2 | 123 | 23 | 547 |
| % | 6.94 | 1.46 | 25.23 | 32.54 | 1.92 | 0.55 | 4.2 | 0.37 | 22.49 | 4.21 | 100 |

**የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ም/ ቤት ተግባርና ሃላፊነት ባጭሩ እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል ።**

- የአገሪቱን በጀት ያፀድቃል፥ በፌዴሬሽን ም/ቤት አማከኝነት በሚቀርበው ቀመር መሰረት ለየክልሎቹ የበጀት ድጎማ ያፀድቃል /ይወስናል/፥ አዋጆችን መርመሮ ያፀድቃል፥ ደንቦችና ከውጭ አገር ያለው ግንኙንት ይወስናል ፥ መመርያ ያወጣል ወዘተ
- በፌዴራል ደረጃ ያሉት የስራ አስፈፃሚ አካላት ሹመት ያጸድቃል እንዲሁም የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ፥ይገመግማል ፥ ይቆጣጠራል ጉድለት ሲገኝም ያርማል ወዘተ

በህዝብ ተወካዮች የትግራይን/ወያኔ ድርሻ ከጠቅላላ 6.9% ነው። ስለዚህ ላየኛው የመንግስት የመዋቅር ስልጣን በወያኔ ነው የተያዘው ብለን ደፍረን መናገር ይቻላልን?

በአገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ደረጃ የሚባልና በቦታው የተቀመጡ የብሄር ስብጥር በሚቀጥለው ሰንጠዥ ይመልከቱ፥

ሰንጠረዥ 3: በከፍተኛ የስልጣን እርከን ያሉ ባለ ስልጣናትና ብሄራቸው

| | የስልጣን ደረጃ | ብሄር |
|---|---|---|
| 1 | የአገሪቱ ፕረዚደንት | ኦሮሞ |
| 2 | የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈ ጉባኤ | ኦሮሞ |
| 3 | ጠቅላይ ሚንስተር | ወላይታ(ደቡብ) |
| 4 | የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ | አማራ |
| 5 | የአዲስ አበባ ከንቲባ | ኦሮሞ |
| 6 | መከላከያ ሚንስተር | ስልጤ (ደቡብ) |

ሌሎች የፌደራል የመንግስት የስልጣን ደረጃዎችም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ከላይ በተጠቀሱት ከፍተኛ ባለስልጣናት በቀጥታ የሚሾሙ /የሚሻሩ ናቸው። ሚኒስትሮች በጠቅላይ ሚንስተር አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንዲፀድቅ ይደረጋል። ከሚ/ር በታች የሆኑ የመንግስት የስልጣን እርከን ደግሞ በጠቅላይ ሚንስተር ይሾማሉ ወይም በተዋረድ ያሉ ባለስልጣናት በስራቸው ያለው የመንግስት የሃላፊነት ቦታ ይሾማሉ። ስለዚህ በወሳኝና ቁልፍ ቦታዎች የትግራይ ተወላጆች የሉም። ታድያ የአገሪቱን ስልጣን በወያኔ ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? ይገርማል?

ከተነሳ አይቀር በፌደራል መስርያ ቤቶች ከሚሰሩት ሰራተኞች ውስጥ ከሚገባቸው በላይ የአንበሳውን ድርሻ ወስደው የሚገኙ የአማራ ተወላጆች መሆናቸው መታወቅ ያለበት ጉዳይ ነው እላለሁ። በፌዴራል መስርያ ቤቶች እስከ 67% የሚሆኑ በአማራ ተወላጆች የተሸፈነ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## የክልል የመስተዳድር ተቋዋማት በተመለከተ

በአገሪቱ ያሉት ዘጠኝ ክልሎች በዋናነት ቋንቋን መሰረት ያደረጉ ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በየክልሉ ነዋሪ በሆነው ህዝብ የየክልላቸው የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላትን ይመርጣሉ። እንዲሁም በየክልሉ የሚቋቋሙት የየክልሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤቶች ለየክልላቸው ከፍተኛው የስልጣን እርከን ናቸው። ብዛታቸውም እንደየክልሉ ሁኔታና ህዝብ ብዛት በየክልሉ ይወሰናል ። በዚሁ መሰረትም በሰንጠረዡ እንደተመለከተው ሰፍረዋል ።

ሰንጠረዥ 4. የየክልሉ የሚውከሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአባላት ብዛት የሚያሳይ

| | ትግራይ | አፋር | አማራ | ኦሮምያ | ቤንሻንጉል | ጋምቤላ | ሶማሊያ | ሃረሪ | ደቡብ ህዝቦች | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ብዛት | 152 | 96 | 294 | 537 | 99 | 155 | 273 | 36 | 348 | |

### የየክልሉ ም/ቤቶች ዋና ዋና የስራ ተግባራት፥

- የክልሉ በጀት ያፀድቃል፥ ከፌዴራል ህገ መንግስት የማይፃረሩ አዋጆች ፥ ደንቦች፥ መመርያ ያወጣል ወዘተ
- በክልል ደረጃ ያሉትን የስራ አስፈፃሚ አካላት ሹመት ያጸድቃል እንዲሁም የስራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፥ ይገመግማል ፥ ይቆጣጠራል ጉድለት ሲገኝ ም ያርማል ወዘተ

ስለዚህ የክልል ርእሰ መስተዳድር (ፕሪዝደንት) በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አማካኝነት ይሾማል። የክልሉ የስራ አስፈፃሚ አካላት በርእሰ መስተዳደሩ አቅራቢነት በክልሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያስፀድቃል። በእርግጥ በርእሰ መስተዳድር የሚሾሙ አካላትም አሉ። ለምሳሌ ም/ቢሮ ሃላፊዎች ፥ የክልሉ የተለያዩ የመንግስት መ/ቤት ሃላፊዎች ወዘተ። የክልል ፕረዚደንት ተጠሪነቱ ለክልሉ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ነው። ስለዚህ በክልልና በፌደራል መስሪያ ቤቶች የሚያገናኝ ድልድይ ህገ መንግስቱና ህገ መንግስቱ ብቻ ነው እንጂ በፌደራል የሚታዘዝ የክልል ባለስልጣን የለም። አንዱ አዛዥ ሌላው ደግሞ ታዛዥ አርጎ አያስቀምጥም። ይልቁንስ ከፌደራል መንግስት ጋር የሚገናኙት በህገ መንግስቱ ላይ በተቀመጠው መሰረት የየድርሻቸው ስራ ይወጣሉ። እንደ አገር ደግሞ በማዘዝና በመታዘዝ ሳይሆን በጋራ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ በጋራ ሁነው ተወያይተው በጋራ ይወስናሉ ።

> **የአንድን ክልል የፀጥታ ጉዳይ ክልሉ ራሱ ይወስናል፣ ያዳራጃል፣ ያስተዳድራል። ችግር እንኳን ቢፈጠር የክልሉ መንግስት ድጋፍ ያስፈልገኛል ብሎ ለፌዴራል ካልጠየቀ የፌዴራል የፀጥታ ሃይሎች ጣልቃ አይገቡም። ስለዚህ አሁን ያለው የመንግስት አወቃቀር የሚያሳየው የፌዴራል ባለስልጣን የሌላውን ክልል ባለስልጣን የማዘዝ ወይም የመሾም መብት እንደሌው በግልፅ ያሳያል።**

በአሁኑ ግዜ ሁሉም ክልሎች ራሳቸው በራሳቸው በማስተዳደር ላይ ባሉበት ሰአት አንዳንድ የአማራ ሊሂቃን ነን ባዮች የሞኝ ዘመቻ ያካሂዳሉ። በትግርኛ አንድ አባባል እንደሚገልፀው “ ዓሻስ ያ ሓንቲ ደርፉ” ወይም ደግሞ “የሞኝ ዘፈን አንድ ነው” እንደሚባለው ሁሌ በኢትዮጵያ የሚደረገው ሁኔታ ከወያኔና ከትግራይ ተወላጆች ጋር ይይዙታል።

ፅሁፌን ከማጠቃለሌ በፊት ኣንድ ነገር ለማለት እፈልጋሎህ። የምናወራው ወሬ ብህዝቦች መካከል ጥላቻንና ዘረኝነትን የሚዘራ መሆን የለበትም። ስለዘረኝነት ያነሳሁበት ምክንያቱ እየተወራበት ሰለሆነ ነው። ዘረኝነት ምን ማለት እንደሆነ ለማሳዬትና ዘረኛ ኣስተሳሰብና ዝንባሌ ያለው ማን መሆኑን ለማስረዳት ነው። ማነው ዘረኛ?

- የነበረውን ብሄራዊ ጭቆና ለማስወገድና ማንነትን ለማስከበር የታገለው ኣካል/ሃይል ወይስ የራስን ማንነት ኣግዝፎ/ከፍ ኣድርጎ የሌላን ሙብት መድፈቅ የሚታገል/የሚፈልግ ?

ለኣሁኑ ያለው ስርዓት መመስረት የነበረው የገዢ መደብና ብሄራዊ ጭቆና ለማለዘብና በህብረተሰቡ ተኣማኒ የሆነ ስርዓት ለመመስረት ነው (ኣንቀፅ 39)። ይህ የፌዴራል ስርዓት በኣግባቡ ካልያዝነው ደግሞ ሊሆን የሚችለው ማሰብ ያስፈልጋል። መታወቅ ያለበት ሁሉም ክልሎች የየራሳቸው የመንግስት መዋቅር ኣላቸው። በመሆኑም

**በኢትዮጵያ ያለን ህዝቦች እንደ ኣገር ኣንድ ላይ ሁነንም ኣንድ ላይ ነን፣ ተለያይተንም በኣንድ ላይ ነን የምንኖረው እላሎህ።**

ስለዚህ በምንም ቢሆን በምንም ቀጣይ የኢትዮጵያ ህዝቦች እጣ ፈንታ መልካም እንዲሆን የምንፈልግ ከሆነ ሁሉም ነገር መሆን ያለበት በመተሳሰብ ነው። ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች እኩል ሙብት እንዳላቸው መቀበልና መተግበር ያስፈልጋል። ለሁሉም ብሄር ብሄረ ሰቦችና እውቅና መስጠት ያስፈልጋል። ካልሆነ ግን እኔ ኣውቅልሃሎህ የሚለውን ቢሂል በኣሁኑ ሰዓት ተቀባይነት የለውም።

**በመጨረሻም በየተኛውም መልኩም ቢሆን ስራዎቻችን ሁሉ መቃኘት ያለባቸው ኣብረን ለማደግ እንጂ ኣብረን ለመውደቅ መራመድ የለብንም እላሎህ። ስለዚህ ከስሜት የፀዳ ኣስተሳሰብ ማንፀባረቅ ከሁሉም ወገን ይጠበቃል እላሎህ።**